# በኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ የቀረበ ትችትና ሐተታ

## ከካሣ ዳምጤና ጓደኞቹ

ትችታችን መነሻ የሆነው በቅርቡ አንድ ፀሀፊ "የገበያ ኢኮኖሚ ወይስ ካፒታሊዝም፤ ወይስ ሌላ...የኢኮኖሚው ጉዳይ አጥጋቢ መልስ ያስፈልገዋል" በሚለው ጽሁፍ ላይ ነው። ፀሐፊው ይህን ርዕስ የመረጡበት ምክንያት እኛን እስከገባን ድረስ በአለፈው "ለምን አይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገለው" በሚለው ጽሁፋቸው ላይ በርካታ አስተያየት፡ ትችትና ጥያቄ ስለቀረቡላቸው መልስና ማብራሪ ለመስጠት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንባብያን ጽሁፋቸውን በደንብ ለመረዳት ያልቻሉት የንቃተ ህሊና ጉድለት ነው ብለው በመገመታቸው፡ አንዳንድ የኢኮኖሚ ጽንስ አሳቦችን ትርጉምና ጥራት ለማስጨበት ጥረት አድርገዋል። በእኛ አስተያየት ጽሁፋቸው ግቡን አለመታም፡ እንደውም ስለ ኢኮኖሚ የጠለቀ እውቀት ለሌለው የበለጠ ብዥታና ውዥምብር ውስጥ የሚጨምር ሆኖ ነው ያገኘነው።

በእኛ ግምት ነገሩ የተበላሸው "ለምን ዐይነት ህብረተሰብ ነው የምንታገው" የሚለው አሻሚና የተምታታ ርዕስ በመምረጣቸው ነው። ምናልባት ርዕሱ "ለማን ነው የምታገለው" ወይም "ለምንድነው የምንታገለው" ወይም "የትግላችን አላማና ግብ ምን መሆን/መምስል አለበት" ቢሆን ኖሮ የጽሁፉ ቅርጽና ይዘት ሳይደበዝዝ ማለት የርዕዮተ ዓለምን ሚና ሳያንኳስስ በተናጠል የኤኮኖሚ ውይይት መሆኑ ይቀር ነበር ባዮች ነን።

ይህን ስንል ርዕስ የመምረጥና ይዘቱን የመወሰን መብት የጸሀፊው መሆኑን በማክበር ነው፡፡ ግን ጥናቱ ለተጨቆነው ሕዝባችን፡ የመኖር መብቱ የተገፈፈበትና በድህነት አረንቋ ውስጥ ለሚዳክረው ከሆነ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትግል ይዘት ያለው ቢሆን ኖሮ ከሚል ምኞት የመነጨ በመሆኑ ይታወቅልን። በጣም ያሳዘነን ጉዳይ ለአለንበት የኢኮኖሚ ቀውስ መፍትሔ ፍለጋ የማይመጥን በመሆኑ ነው። በእኛ አስተሳስብ አንድን አስተማሪ/ፕሮፌሰር ጎበዝ የሚያስኘው ለህብረተስቡ የፖለቲካ፡ የኤኮኖሚና የማህበራዊ (የሶሻል) ችግሮች/ቀውሶችን በቀላሉ እንዲረዱት ማድረግ ሲችል ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድን የተወሳሰበ ጽንስ አሳብ ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ ለማስተማር/ለማስረዳት መቻል ነው። ለህብረተሰቡም በቂ ግንዛቤ

ከአስጨበጠ በኋላም በመፍትሔው ፍሊጋ ላይ በሙሉ ልብ ዳተኛ ሳይሆን እንደዜጋ ሊሳተፍ ሲችል ሀላፊነቱን በበቂ ተውጥቷል ማለት ነው።

ጸሀፊው ለአንባቢዮቻቸው ያቀረቡትን አንኳር አሳቦች በእኛ እይታ በአንድ ላይ ተድበልብለው ነው የቀረቡት። የሚጀምሩት እንደ የኢኮኖሚክስ 101 ትምህርት ሳይሆን ከከባድ ሀተታና ትንተና ነው። በአንድ ላይ ተድበልብለው የቀረቡት፦

1. ከግሎባል ኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ በኢኮኖሚና በነፃ ገበያ ጽንሰ አሳቦች መካከል ያለውን ልዩነትና ግንኙነት ለማስረዳት ቢሞክሩ እያንዳንዳቸውን በጽንስ አሳብ ደረጃ ምን ማለት እንደሆኑና እንዴትስ እንደሚገናኙ ቢደረግ ኖሮ ይቀል ነበር።

2. በነፃ ገበያና በካፒታሊዝም መካከል ያለው ልዩነትና ግንኙነት መግለጽ መልካም ሆኖ ሳለ ነፃ ገበያ ለድሃ አገሮች ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል የሚለውን ጉዳይ ምንም ሳይገለጽ ተዘሎአል።

3. ኒዮሊበራልና የገበያ ኢኮኖሚ ትስስር አለው? ከሆነስ ለምን ለአሁኑ የፋይናስ ገበያ ቀውስ ተጠያቂ አይሆንም? ምናልባት ሳይገባን ቀርቶ ከሆነም እንዴት ኒዮሊብራል የፍትሃዊ ገበያ ተሟጋች መስሎ ለመቅረብ አስፈለገ? የሚለውን ማንሳቱ የግድ ይሆናል።

4. ጸሀፊው ግራ መሰል መሆናቸው ብዙ አነጋጋሪ ሆኗል። በእኛ አስተያየት መሆንና መምስል መካከል ያለው ልዩነት ትልቅ ነው። በጣም ግራ የሚያጋባው በአሁኑ ወቅት "ከፊውዳሊዝም ወደ ሶሻሊዝም" እንግባ ሳይባል ካፒታሊዝም ልናልፈው የማንችለው ስርዓት ነው የሚለውን አሳብ ምን አመጣው? ስለ ሶሻሊዝም ማለት የእዝ ኢኮኖሚ በሚለው ላይ ለመወያየት ከተፈለገ ለምን በግልጽ እንደ ርዕስ ሆኖ አልቀረበም? ያን ያህል ስለ ኒዮሊብራሊዝምና ስለ ነፃ ገበያ ሲወራ ለምን ስለ ሶሻል ዴሞክራሲና የገበያ ኢኮኖሚ ማለት ለቅይጥ ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ትግል በጽሁፉ ውስጥ አልተጠቀስም? ስለድህነትና ረሃብ እንዲሁም መፍትሔ ማቅረብ ትኩረት ተስጥቶት አልቀረበም።

ያገር ጉዳይ ሲነሳ አብዛኛው ምሁር ነኝ ባዩች የሚቀናቸው "እኔ የማንም ወገን ወይም የፓለቲካ አቅዋም ደጋፊ ወይም አራማጅ አይደለሁም" ማለቱ በእኛ አስተያየት አጸያፊ ነው። በተለይ በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ችግርና ጥፋት መኖሩንና መታረም እንዳለበት ቢያምኑም ግን ማንንም ላለማስቀየም ማለት በአድርባይነት ትችትና ሂስ የሚስነዝሩት የጅምላ ወቀሳና ፍሬፈርስኪና

ግማሽ እውነትና ግማሽ ውሸት ማውራት ይቀናቸዋል። አንዳንድ ምሁር ነን ባዮች የሚበቃቸውን ከለፈለፉና ውዥንብርና ብዥታ ከለቀለቁ በኋላ ጠንከር ያለነገር ሲመጣ ዘወር ብለው ይጠፋሉ። በመሆኑም ሕዝባችን በተለይም በአወናባጅ ምሁራን የተነሳ በአጠቃላይ ምሁር ላይ ተስፋ እንዲቀርጥ ረግረግ ያመቻቸ ነው ለማለት ወደሚያስደፍር ደረጃ ተደርሷል።

በአንጻሩ ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ምሁራን ለሚያምኑበት ጉዳይ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ናቸው ብለን እንገምታለን። በአሁን ቀውጢ ጊዜ የሚያስፈልገን ያለንበትን የኢኮኖሚው ቀውስን ለመቋቋምና ለማስወገድ እንደሕዝብ ምን ማድረግ አለብን? ብለን መወያየትና የአሳብ ፍጭቶች ማድረግ እንችላለን ብለው ይጨነቃሉ፥ ይጠበባሉ። እኛም የፓለቲካ አቅዋም መኖር ለፍትሃዊ የኤኮኖሚ ትግል የአሳብ ጥራት ይረዳል ብለን እናምናለን። ሀገር ወዳድ ምሁራን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ መታገልና ማታገል ያለባቸው የተቀደሰ ተግባር ነው። በተጨባጭ እለት በለት የምናየውና የምንሰማው አገር በቀል (organic intellectuals) ወገንተኛ ሆነው ማለት የለውጥ ሐዋርያ ሲሆኑ በአንጻሩ ደግሞ ፈረንጅ አምላኪ (inorganic intellectuals) ምሁራን ያለውን ስርዓት እንዳይለወጥ/እንዳይነካ ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ መሆናቸውን ነው። በአጠቃላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የአሳብ ፍጭት በማድረግ የአመለካከት ጥራት መኖርና እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ትግል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለእንዲህ ያለ ትግል ደግሞ ርዕዮተ ዓለም፥ ራዕይና መርሃ ግብር መኖራቸው ወሳኝ ነው። ስለሆነም በቅጡ ከተረዳንዎ እርሶን መሰል የህብረተሰብ ምሁር ከማንም ሳልወግን ያለንበትን የኤኮኖሚ ቀውስ እንዲያው እውቀት ለማፍለቅ ብቻ እመራመራለሁ ማለት አላፊነትን መሸሽ መስሎ ነው የሚታየን። እውቀትን እንደእውቀት መመራመሩ መጥፎ ነው ባይባልም ወደፊትም አስፈላጊነቱ እስከሚመጣ ድረስ አሁን አገራችን በመኖርና ባለመኖር በአለችበት ወቅት እንዲህ ያለ ክርክር መግጠሙ ማለት "ንፁህ ምሁራዊ ትግል" እናድርግ ማለቱ ቅንጦት ይሆናል ብለን እናስባለን።

የኤኮኖሚ ጥናት ግን የጸሀፊው አባባል እንዋስና "ተጠላም ተወደደ" ከርዕርዮተ ዓለም ውጭ ሊሆን አይችልም፥፥ ፍልስፍና ምናልባት እንደሁኔታው ከርዕዮተ ዓለም ውስጥም ውጭም ሊሆን ይችላል። ያም ሆኖ ፈላስፎች ለህብረተሰብ የእድገት የሚያበረክቱት ጽንሰ አሳቦች ወደፊት ስላምና የተረጋጋ ሁኔታዎች በትግላችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲፈጠር መበረታታ ያለበት ነው ባዮች

ነን። ስለዚህ አገራችን የሚያስፈልጋት ንፁህ የኤኮኖሚ ጥናት ሳይሆን አታጋይ የፖለቲካል ኤኮኖሚ ጥናታዊ ውይይትና የአሳብ ፍጭት ነው። ከዚህ ውጭ የንፁህ ሰብአዊነት ትግል ምን ማለት እንደሆነ ግር ያሰኛል። ትርጉሙ ለመብት ትግል ማለት ነው? ለመብት ከሆነ በሙሉ ልብ እንደግፋለን ማለት አንድ ሰው ማንም ምን ይሆን በፖለቲካ አመለካከቱ ምንም አይነት እንግልት ሊደርስበት አይገባም። በመሆኑም የስብአዊ መብት ተሟጋቾች ወገንተኛ ሳይሆኑ ሃሳባቸውን በግልጽ በማቅረባቸው የተነሳ ለእስር የተዳረጉ ሁሉም እስረኞች እንዲፈቱ መጮህና መታገል አግባብነት ያለው ነው።

ጸሀፊው በጽሁፋቸው ውስጥ ስለአውሮፓ አገሮች ፈላስፎችና አሁን ያሉት የእድገት ደረጃ እንዴት እንደደረሱ ለአንባቢያን ለማሳየት ጥረት አድርገዋል። በተመክሮ ደረጃ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ያም ሆኖ ሳይብራሩ ያለፉት ከ17ኛውና ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት አውሮፓ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ በሚኖሩበት ዘመን ኢትዮጵያ የተሻለ ሥልጣኔ እንደነበራትና ኢትዮጵያዊ የራሷ ፈላስፋ ዘርዓያቆብ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ስለተፈጥሮ፡ ስለ እምነት ማለት በካቶሊክና በኦርቶዶክስ ቀኖና መካከል ልዩነትና አንድነት፡ ስለእውነት፡ ስለህግና አስተዳደር መመራመሩንና በምርምሩም በራሱ ግኝታ ሀተታና ትንተና (analysis and synthesis) ለዓለም ህብረተሰብ ማበርከቱን መርሳት የለበትም እንላለን። አውሮፓ እንዴት እንዳደገች ሲያውሱ ሳይገለጥ የታለፈ ነገር እንግሊዝን በምሳሌነት ብንወስድ በአህጉር ደረጃ አሜሪካንን፡ አውስትራሊያን፡ የእስያ አገሮችን እንደ ህንድና ቻይና እንዲሁም አብዛኛውን የአፍሪቃ አገሮች በቅኝ ገዢነትና በተጨማሪም በባርያ ፍንገላ ተግባር ባትሰማራ ኖሮ ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር የሚያስፈልገውን የነፃ የሰው ጉልበትና ጥሬ እቃዎች ተየት ታመጣ/ታገኝ ነበር?

አንድ የምንስማማበት ቁምነገር ፀሀፊውና ትችት አቅራቢዮች በአንድ ህብረስብ ውስጥ አመርቂ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል ለውጥ ለማምጣት የርዕዮተ ዓለምና የንድፈ አሳብ (ቲዮሪ) ጥራት አስፈላጊ መሆኑን ነው። ይህ አሳብ እውን ለማድረግ ከምኞት ባሻገር ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ሁለገብ ትግል በማድረግ ነው። ርዕዮተዓለም አላማና ግብ ያለው ማለት የፖለቲካ፡ የኤኮኖሚና የሶሻል ችግሮችን ለማስወገድ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የተቀመሩ አሳቦችን ያካተተ ነው። ትግል በሚካሄድበት አገር ነባራዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ካልተገኙ የአብዮታዊ ምሁራን (social scientists) ማለት ለውጥ ፈላጊዎች ሚና የሚሆነው አቅጣጫ የሚጠቁሙ ንድፈ አሳቦች

መሻት ወይም ማፍለቅ ነው። በአንጻሩ ሆድ አደር (አድርባይ) ምሁራን ያለውን ሥርዓት ሲቻል በቀጥታ በመደገፍ ሳይቻል በሕዝብ ዘንድ ውዥንብርና ብዥታ ያለው ቅስቀሳ ወደ ማስራጨቱ ይሰማራሉ ማለት ነው።

ዓለም ከተፈጠረ አንስቶ ምናልባት ከጋርዮሽ ሥርዓት በፊት የመደብ ክፍፍልና ትግል አልነበረም ማለት ይቻል ይሆናል ብለን እንገምታለን። ከዚያ በተረፈ ከባርያ ሥርዓት ጀምሮ በባሪያና በባሪያ አሳዳሪ፡ በፊውዳል ሥርዓት ንጉስ፡ ንጉሳዊ ቤተሰብ፡ ባላባቱ፡ መኳንንቱና ባለትልልቅ መሬት ባለቤቶች በአንድ በኩል በተቃራኒው ደግሞ ሰፊው አርሶ አደሩ፡ መጫኛ ነካሹ ነጋዴ፡ ቀጥቃጩ፡ ሸክላ ስሪው የመደብ ትግልና ክፍፍል ነበራቸው። ሌላው ሁላችንም የምናውቀው በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ባለ ሀብት(the haves)ና ምንም የሌለው መናጢ ደሃ (the have-nots) ጉልበቱን ሸጦ በሚተዳደረው መካከል የመደብ ክፍፍልና ትግል በመካሄድ ላይ ነው። ያለፉት ሥርዓቶችና የአሁኖቹን ጨምሮ የየራሳቸው የሚመሩበት ርዕዮተ ዓለም ነበራቸው ያሁኖቹም አላቸው። የሁሉም ሥርዓት በየጊዜያቸው ተራማጅና አድሃሪ ፈላስፋዎችና ምሁራን ነበሯቸው። ርዕዮተ ዓለምን በጽንሰ አሳብ ድረጃ ሆነ ለተግባራዊ ስምሪት የተፈጠሩት በሂደት እንጂ የግራና የቀኝ አስተሳሰብ ያላቸው ግለስቦችና ቡድኖች ወይም ፓርቲዎች አይደሉም፤ ግን አዳበሩት ሊባል ይቻላል። ለማጠቃለል የወደፊት ጥናት ጽሁፎች ስለሶሻሊዝምና ካፒታሊዝም እንዲሁም የሁለቱ ቅይጥ (social democracy) እንደ ሥርዓትና ስልተምርት የሚያብራራ ቢሆን ጥሩ ነው እንላለን። የገበያ ኢኮኖሚና የዕዝ ኢኮኖሚ እንዲሁም ቅይጥ ኢኮኖሚ በዝርዝር መመርመሩ ጠቃሚ ነው ብለን እናስባለን። በተረፈ ብዙ መንዛዛት እንዳይሆንብን ስለ ግሎባላይዜሽን ርዕዩትነት፡ እድገትና ሂደት፡ እንዲሁም ሶሻል ዴሞክራትና ሊብራል ዴሞክራት  በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ በምን ላይ እንደሚለያዩና እንደሚተባበሩ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረን በፍካሬ መጽሔት ቅጽ 15፣ ቁጥር 1፣ ህዳር 2000 ዓ. ም. የስፈረውን እንድትመለከቱ በአክብሮት እንጠቁማለን።

በአጭሩ ከጸሀፊው ጋር ያለን ልዩነት ማለት በንፁህ የኤኮኖሚ ጥናት ላይ እናተኩር ከሚለው አማራጩ የፓለቲካል ኢኮኖሚ ጥናትና ውይይት ቢሆን የተሻለ ነው።  ስለሆነም ውይይቱ ጤናማ እስከሆነ ድረስ መቀጠል አለበት እንላለን።